መግቢያ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ ኤፍሲ-ሄረንደን የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ሲሆን ማህበሩ ሰራተኞች ያቋቋሙት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመረዳጃ መኅበር ነዉ።

1. አንቀጽ አንድ

1.1. የማኅበሩ መጠሪያ

ይህ ማኅበር ኤፍሲ-ሄረንደን ሠራተኞች መረዳጃ ማኅበር ተብሎ ይጠራል።

2. አንቀጽ ሶስት

2.1. የማኅበሩ ዓላማ

የማኅበሩ ዓላማ በአንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 6.1 እና በአንቀጽ 5.3. ሀ) የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ላይ በመመስረት ለአባላቱ በችግር ጊዜ መጠነኛ የሆነ የአንድ ጊዜ ድጋፍ በማድረግ ሊደርስባቸዉ የሚችለዉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለማቃለል ነዉ።

3. አንቀጽ አራት

3.1. የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

የማኅበሩ የገቢ ምንጭ ከአባላት የሚሰበሰብ የአንድ ጊዜ መመዝገቢያና ቋሚ ወርኃዊ መዋጮ ነዉ።

4. አንቀጽ አምስት

4.1. አባልነትን በተመለከተ

ሀ) አባላቱ የመመዝገቢያ በአንድ ጊዜ የሚከፈል $100.00 (አንድ መቶ ዶላር) ያዋጣሉ።

ለ) አባላቱ በየወሩ $20 ያዋጣሉ፤ ወደፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመዋጮዉ መጠን ሊሻሻል ይችላል::

ሐ) የፌርፋክስ ኮኔክተር ሄረንደን ነባር ተቀጣሪ ሆኖ እና ይህ ማኅበር ሲመሰረት አባል ሳይሆን ቀርቶ ዘግይቶ እስከ 8 ወር የሚቀላቀል አባል እስከዛን ጊዜ ድረስ የተዋጣን ወርሃው መዋጮ ድምር እና የመመዝገቢያ $100 ከፍሎ ይገባል::

መ) የፌርፋክስ ኮኔክተር ሄረንደን አዲስ ተቀጣሪ ሰራተኛ የማህበሩ አባል ለመሆን ከፈለገ በተቀጠረ በሶስት ወራት ውስጥ የአባልነት ጥያቄውን ለማህበሩ ካቀረበ ወርሃዊ መዋጮና $100 መመዝገቢያ ከፍሎ ይገባል። የአባልነት ጥያቄውን ከተቀጠረ ሶስት ወራት በኋላ ካቀረበ ግን በንኡስ አንቀጽ ሐ) እና ሠ) መሰረት የሚስተናገድ ይሆናል።

ሠ) ይህ ማኅበር ከተመሰረተ በኋላ ፌርፋክስ ኮኔክተር ሄረንደንን ከተቀላቀለ ከ8 ወራት በኋላ የአባልነት ጥያቄን የሚያቀርብ አዲስ አባል **$300.00 (ሦስት መቶ ዶላር) መመዝገቢያ ይከፍላል፤** የአባልነት ወርሃዊ መዋጮውንም አባል ከሆነበት ወር

ጀምሮ ይከፍላል።

ረ) ማንኛውም አባል አገልግሎት ማግኘት የሚችለው በአባልነት ከተቀላቀለ ከ3 (ሶስት) ወራት (90 ቀናት) በኋላ ይሆናል። አባሉ አባል ከሆነ ጀምሮ እስከ ሶስት ወር (90 ቀናት) ደረስ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ምንም አይነት ድጋፍ አያደርግም።

ሰ) ማንኛውም ሰራተኛ የማኅበሩ አባል ሲሆን ይህን የመተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎና በደንቡም ለመገዛት ተስማምቶ ነው።

ሸ) ሁሉም ሰራተኛ የማኅበሩ አባል ሲሆን የዚህን መተዳደሪያ ደንብ ኮፒ ፈርሞ መቀበል ይኖርበታል።

4.2. አባልነትን ስለመተው ወይም ማቋረጥ በተመለከተ

ሀ) አንድ አባል መዋጮ እስከከፈለ ድረስ ከፌርፋክስ ኮኔክተር ሄረንደን ሥራ ቢለቅ ወይም ሥራ ቢቀይር በማኅበሩ አባልነት መቀጠል እስከ ፈለገ ድረስ እንደማንኛዉም አባል ጥቅሙ ይጠበቅበታል። ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው ከፌርፋክስ ኮኔክተር ሄረንደን የለቀቁና በአባልነት ለመቀጠል የፈለጉ አባላት ቁጥር IRS ከሚፈቅደው 10% እስካልበጠ ደረስ ብቻ ይሆናል።

ለ) አንድ አባል በማኅበሩ ዉስጥ መቀጠል ባይፈልግ በማናቸዉም ጊዜ እራሱን ከማህበሩ ማግለል ይችላል። ሆኖም ግን ከማኅበሩ በሚለቅበት ወቅት ማኅበሩ በባንክ ተቀማጭ ገንዘብ ቢኖረዉ ይህ ሰዉ ድርሻ መጠየቅ አይችልም፤ መካፈልም አይችልም።

4.3. ዝርዝር ደንብ (የአባሉ የቅርብ ቤተሰብን በተመለከተ)

ሀ) የአባሉ የቅርብ ቤተሰብ ማለት፥ የአባሉ (አባሏ) ሚስት/ባል፣ ልጅ፣ እናትና አባት ብቻ ናቸው።

5. አንቀጽ ስድስት

5.1. ያጋጠመን ችግር ስለማሳወቅ

ሀ) አንድ አባል በማንኛውም ምክንያት ከሥራ ቢሰናበት (ቢባረር)፤ በህመም ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ከስራው ታግዶ ቢቆይ ወይም ከላይ በአንቀጽ 5.3. ሀ) ከተጠቀሱት መካከል የቅርብ ቤተሰብ ቢሞትበት ከ60 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተከሰተውን ችግር ለዚሁ አላማ የተዘጋጀውን የክሌም ፎርም በመሙላት ለኮሚቴዉ የማሣወቅ ግዴታ አለበት።

6. አንቀጽ ሰባት

6.1. ኮሚቴን በተመለከተ

ሀ) የስራ አስፈጻሚ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነሱም ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ኦዲተር፣ ጸሐፊና ገንዘብ ያዥ በመሆን የማህበሩን የእለት ተእለት ጉዳዮችን ያከናውናሉ።

ለ) ማኅበሩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን በየሁለት ዓመቱ ይመርጣል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ከአባሉ መካከል 2/3ኛና ከዚያ በላይ ሲያምንበት አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ የማሚያ ወይም ሙሉ ምርጫ ሊካሄድ ይችላል።

ሐ) አሁን ያለዉ ኮሚቴ ይህ ሠነድ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ይቀጥላል፤ የሥራ ድርሻ ክፍፍል በማድረግም

ለማኅበሩ ያሳዉቃል።

መ) ማንኛውም አባል በማኅበሩ የስራ አስፈጻሚነት ቦታ እንዲያገለግል ቢመረጥ አሳማኝ ምክንያት ከለሌ በስተቀር ኃላፊነቱን ተቀብሎ ማገልገል የአባልነት ግዴታ አለበት።

ሠ) አንድ አባል በማህበሩ ስራ አስፈጻሚነት ለማገልገል በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም።

7. አንቀጽ ስምንት

7.1. ስለመዋጮ አሰባሰብ

ሀ) መዋጮ የሚሰበሰበዉ ወር በገባ (በፈንጅች አቆጣጠር) ከ ፡- 10 ባሉት ቀናት ይሆናል። አንድ አባል በዚህ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ካልከፈለ ተጨማሪ $10 መቀጫ በመጨመር $30 እንዲከፍል ይገደዳል።

ለ) ሆኖም አባሉ ወርሃዊ ክፍያውን ሳይከፍል ወሩ ቢያልቅ እና የሚቀጥለው ወርም የመክፈያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ክፍያውን ከነቅጣቱ ሳይከፍል ቢቀር ተጨማሪ $10 ቅጣት በጠቅላላ $20 ቅጣት እና ያልከፈለውን የሁለት ወር ወርሃዊ መዋጮ $40 በማድረግ በአጠቃላይ $60 ይከፍላል።

ሐ) ከላይ በአንቀጽ 5.2. ንኡስ አንቀጽ ለ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አባሉ ለሶስት ተከታታይ ወራት ግዴታውን ሳይወጣ ቢቀርና ሶስተኛ ወሩ ላይ ወርሃዊ መዋጮውን ከነቅጣቱ መዋጮ በሚሰበሰብበት የጊዜ ገደብ አጠቃሎ መክፈል ካልቻለ አባልነቱን በፈቃዱ እንደተወ ይቆጠራል፤ ከዚያ በኋላ ምንም አይነት አገልግሎትም አያገኝም።

መ) ከላይ በአንቀጽ 5.2. ንኡስ አንቀጽ ለ) ወይም በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሐ) በተጠቀሱት ምክንያቶች አባልነቱን የተወ አባል ድጋሚ አባል ለመሆን ጥያቄ ካቀረበ አባልነቱን ካቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ያልተከፈለ ወርሃዊ የባልነት መዋጮና $50 መቀጫ ከፍሎ አባል ሊሆን ይችላል። ሆኖም አባሉ የሚከፍለው ውዝፍና ቅጣት ተደምሮ ከ$300 መብለጥ የለበትም።

8. አንቀጽ ዘጠኝ

8.1. ስለ ገንዘብ አስተዳደር

ሀ) ኮሚቴዉ የባለ ሦስትዮሽ ፊርማ የባንክ ሂሳብ በማኅበሩ ስም ይከፍታል የሚዋጣዉም ገንዘብ በዚሁ ሒሳብ ይጠራቀማል

ለ) የገንዘብ አወጣጡም በ3ቱ የኮሚቴ አባላት ፊርማ ይፈፀማል

ሐ) የወጪና የገቢ ሚዛን (Balance Sheet) በየወሩ መጨረሻ ተዘጋጅቶ ለአባለቱ ይገለጻል።

9. አንቀጽ አስር

9.1. የድጋፍ አደራረግ ሂደት

ሀ) አንድ አባል በማናቸውም ምክንያት ከስራ ቢሰናበት (ቢባረር) እና የሰራተኛ ማህበር የይግባኝ አቤቱታ ተሰምቶና የአባሉ ስንብት የመጨረሻ መሆኑ ሲረጋግጥ **የ2,500** ድጋፍ ያደርጋል።

ለ) አንድ አባል በማንኛውም ምክንያት ከ30 ቀናት በላይ ከሥራ ታግዶ ወይም በሕመም ምክንያት ከ30 ቀናት በላይ ከስራ ውጪ ቢሆንና ይህንንም ጊዜ ያለ ከፍያ የቆየ እንደሆነ ማኅበሩ ከተሰበሰበዉ ገንዘብ ላይ **$ 1,500** የአንድ ጊዜ

ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ሆኖም በFMLA ከሥራ ገበታ ውጪ ለሆነ አባል ማኅበሩ አባል ምንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ አያደርግም።

ሐ) አንድ የማህበሩ አባል ከዚህ አለም በሞት ቢለይ ማህበሩ ከማህበሩ አካውንት ወጪ በማድረግ **የ$5,000** እና በተጨማሪ ከእያንዳንዱ አባል ተጨማሪ $100 በመሰብሰብ ከማህበሩ አካውንት ላይ ወጪ ከተደረገው ጋር በመደመር አባሉ/ሏ ለሰየመው/ችው ድጋፍ ተቀባይ ያስረክባል። ከአባላት የሚሰበሰበው **$100** የሁሉም አባላት ግዴታ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ማድረግ የሚፈልግ አባል ቢኖር በግሉም ሆነ በማህበሩ በኩል ተጨማሪውን ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል።

መ) አንድ አባል በአንቀጽ 5.3 ሀ) ስር ከተጠቀሱት የቅርብ ቤተሰብ አባላት መካከል፡-

- ⇨ የአባሉ/ሏ እናት ወይም አባት ከዚህ አለም በሞት ቢለዩ ማህበሩ ለአባሉ/ሏ **የ$2,000** ድጋፍ ያደርጋል
- ⇨ የአባሉ/ሏ ሚስት/ባል ወይንም ልጅ ከዚህ አለም በሞት ቢለይ ማህበሩ ለአባሉ/ሏ **የ$3,000** ድጋፍ ያደርጋል።

ሠ) ለማህበሩ አባላት በችግራቸው ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ማህበሩ ለባሉ/ሏ በአካል በቅርብ በመሆን የሚያግዙና ጉዳይ የሚፈጽሙ አባላት ይመድባል። በሀዘን ጊዜ በሀዘንተኛው ቤት በመገኘት የማጽናናት ተግባር የሁሉም አባላት ማህበራዊ የውዴታ ግዴታ ነው።

ረ) አንድ አባል ልጅ ቢወልድ፣ ቢያስመርቅ ወይም እራሱ ቢመረቅ ቤት ቢገዛ ይህ ማኅበር ምንም ድጋፍ አያደርግም።

ሰ) በአባሉ ወይም በአባሉ የቅርብ ቤተሰብ ላይ የደረሰውን ችግር በማስመልከት የድጋፍ መጠየቂያ ፎርም በአባሉ ወይም አባሉ ራሱ በሰየመው ወይም በህግ በታወቀ የአባሉ ህጋዊ ተጠቃሚ ሰው ተሞልቶ መቅረብ አለበት።

10.አንቀጽ አስራ አንድ የተጠቃሚ (ተጠቃሚዎች) ስያሜ

10.1. የመጀመሪያ ተጠቃሚ ስያሜ

ሀ) እያንዳንዱ አባል ወደ ማህበሩ በሚቀላቀልበት (በሚመዘገብበት) ወቅት ተጠቃሚ መሰየም አለበት። ስያሜው ማህበሩ ባዘጋጀው ይፋዊ የ“አባላት መመዝገቢያ እና ተጠቃሚ መሰየሚያ ቅጽ” ላይ በጽሁፍ መሆን ይኖርበታል። የተሰየመው ተጠቃሚ በዕቅዱ (ፕላኑ) መሰረት የሚከፈለውን ማንኛውንም የሞት ጥቅማጥቅም የመቀበል ሙሉት ይኖረዋል።

10.2. ተጠቃሚን ስለመቀየር

ሀ) ማንኛውም አባል የተሰየመ ተጠቃሚን በማንኛውም ጊዜ ለመቀየር ወይም ለማሻሻል ይችላል፤ ይህንንም ለማድረግ ተሞላ የ“ተጠቃሚ መቀየሪያ ቅጽ” ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ማቅረብ ይኖርበታል። ለውጡ የሚፀናው በማህበሩ ደርሶ ዕውቅና ሲሰጠው ይሆናል።

10.3. መዝገብ አያያዝ

ሀ) ማህበሩ ሁሉንም የተጠቃሚ ስያሜ እና የለውጥ ቅጾችን እንደ ይፋዊ የአባላት መረጃ መዝገብ አካል አድርጎ ይይዛል።

11. አንቀጽ አስር

11.1. ልዩ ልዩ ጉዳዮች

ሀ) አባላቱ በዓመት አንድ ጊዜ ተገናኝተዉ ሪፖርት ያዳምጣሉ ይወያያሉ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ማሻሻያዎችን አቅርበዉ እንዲተገበር ያደርጋሉ፡፡

ለ) ለአንድ አባል ድጋፍ ለማድረግ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ቢፈጠሩ ማለትም ከላይ በአንቀጽ 10.1 ንኡስ አንቀጽ ሀ) እስከ መ) የተጠቀሱት ሁኔታዎች ቢከሰቱና ድጋፉን ለማደረግ የሚያስችል የገንዘብ መጠን በማኅበሩ አካውንት ውስጥ ባይኖር የማኅበሩ ስራ አስፈጻሚ የሚወስነውን መጠን እያንዳንዱ አባል ከኪሱ የማዋጣት ግዴታ አለበት።

12. አንቀጽ አስራ ሁለት

12.1. የካፒታል ክምችት ገደብ፣ የመዋጮ እረፍት እና መዋጮ እንደገና ስለመጀመር

ሀ) ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ገደብ፡- ማህበሩ ከፍተኛው የካፒታል ክምችት መጠን $45,000.00 (አርባ አምስት ሺህ ዶላር) ይወሆናል።

ለ) ወርሃዊ መዋጮን ስለማቆም፡- የካፒታል መጠኑ $45,000.00 (አርባ አምስት ሺህ ዶላር) ሲደርስ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው "የመዋጮ እረፍት" (Contribution Holiday) ያውጃል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ወርሃዊ መዋጮ ለጊዜው ይቆማል። ሆኖም ግን አዲስ ለሚመዘገቡ አባላት የአባልነት ምዝገባ ክፍያ አሁንም ተፈጻሚ ይሆናል።

ሐ) መዋጮን ስለመቀጠል፡- የካፒታል መጠኑ ከ $35,000.00 (ሰላሳ አምስት ሺህ ዶላር) በታች ሲወርድ የ30 ቀናት ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት መደበኛው ወርሃዊ መዋጮ እንደገና እንዲቀጥል ይደረጋል።

13. አንቀጽ 13፡ ማሻሻያ እና ማህበሩን ስለማፍረስ

ሀ) ተጨማሪ መዋጮ (Assessments)፡- ለማህበሩ አባላት የግዴታ ክፍያዎችን ለመፈጸም በካዝናው ውስጥ ያለው ገንዘብ በቂ ካልሆነ ኮሚቴው ክፍተቱን ለመሙላት በአባላት ላይ ተጨማሪ መዋጮ ሊያዝ ይችላል።

ለ) ማህበሩ ስለሚፈርስበት ሁኔታ፡- ማህበሩ በሚፈርስበት ጊዜ (ከዕዳ እና ግዴታዎች ክፍያ በኋላ) የቀረው ማንኛውም ንብረት እና ገንዘብ በአባላቱ አብላጫ ድምፅ ውሳኔ ለበጎ አድራጎት ድርጅት (501(c)(3)) ይለገሳል። ከማህበሩ ንብረት ውስጥ ለማንኛውም ግለሰብ የግል ጥቅም የሚውል ምንም ዓይነት ሀብት አይኖርም።

14. አንቀጽ አስራ አንድ

1.1. ስለ መመስረቻ ደንብ መጽደቅና መሻር በተመለከተ

ሀ) ይህ የማህበሩ መመስረቻ ደንብ በፈንጅች አቆጣጠር ከጥር 1, 2026 ጀምሮ የጸና ይሆናል።